# ሰርድሚል ተቋም
## የደቀመዝሙርነት ባጅ

*ሁሉንም እንዲህ አላቸው፡- "ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል።*

ሉቃስ 9፡23-24

ክርስቲያናዊ ደቀመዝሙርነት ኢየሱስን መከተል እና በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ በእርሱ ማደግ ነው። ይህን ስንል ስለ ብዙ አይነት እድገት ሊሆን ይችላል። ስለ ባህሪ አፈጣጠር ሊሆን ይችላል። በቅዱሳት መጻሕፍት ባለን እውቀት ማደግ ሊሆን ይችላል። የክርስቶስን ፍቅር እና መልእክት ለሌሎች ለማዳረስ አስፈላጊ የሆኑትን ክህሎቶች ማዳበር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሁልጊዜም ቢሆን እንደ ተማሪ እና ተከታይ ሆኖ ከኢየሱስ ጋራ በመፍራት እና በትህትና መመላለስ መሆኑ እርግጥ ነው። *ይህንንም* ደግሞ አብረን እናደርጋለን። ከተፈለገው ግብ በመነሳትና እና በምትኖርበት ቦታ ላይ በመመስረት ደቀ መዝሙር የማድረግ ሂደቱ ሊለያይ ይችላል። በዚህ ባጅ ፣ በደቀመዝሙርነት የማድረግ ሂደት ውስጥ መካተት ያለባቸው ክፍሎች ምን መሆን እንዳለባቸው እና የት እና እንዴት ለሌሎች ማድረግ እንደሚችሉ ይወያያሉ።

### ባጁ የሚያጠቃልለው - የውይይት ርዕሶች ከእነዚህ ሶስት አቅጣጫዎች ይመጣሉ፡-

**ባህል** - በምትኖሩበት ቦታ ደቀ መዝሙር ማድረግ
**ቤተ ክርስቲያን** - እግዚአብሔር በጠራችሁ ቦታ ሆናችሁ ደቀ መዝሙር ማድረግ
**ግላዊ** - እግዚአብሔር ሲጠራህ እንድትሆንለት የፈለገውን ደቀ መዝሙር መሆን

### የውይይት ርዕሶች፡-

1. በአገራችሁ ደቀመዝሙርነት ምን ይመስላል?
2. ሌላ ሰው ደቀ መዝሙር ስታደርጉ የምታካትቱት ዋና ዋና ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
3. ሰዎች ከክርስቶስ ጋር ሲሄዱ በአካሄዳቸው እንዴት እያደጉ የሄዳሉ?
4. ደቀመዝሙርነት ምን መምሰል እንዳለበት ለማሰብ የትኞቹን የቅዱሳት መጻሕፍት ምሳሌዎች ልንጠቀም እንችላለን?
5. በአሁኑ ጊዜ በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደቱ ምን ይመስላል? የደቀመዝሙርነትን ሂደት የሚያሳይ ሥዕል/ሥዕላዊ መግለጫ ይሳሉ።
6. በደቀመዝሙርነት ላይ ያተኮሩ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ዘርዝሩ።
7. የደቀመዝሙርነት ፕሮግራም በማዘጋጀት ረገድ የትኞቹን የሕይወት ክፍሎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል?
8. በዮሐንስ 15 ላይ ኢየሱስ ስለ የትኞቹ ትእዛዛት ነበር የተናገረው?
9. ደቀመዝሙርነት ስለ ባህሪ አፈጣጠር ወይም የመንፈስ ፍሬ ስለማፍራት የሆነው እንዴት ነው?
10. በአንድ ጊዜ ስንት ሰዎች ደቀ መዝሙር ማድረግ ይችላሉ/ይገባል?
11. መጽሐፍ ቅዱስ በደቀመዝሙርነት ሂደት ውስጥ ምን ቦታ ሊኖረው ይገባል (ማንበብ፣ ማጥናት፣ ማስታወስ፣ ወዘተ)?
12. ጸሎት በደቀመዝሙርነት ሂደት ውስጥ ምን ቦታ ሊኖረው ይገባል?
13. በቤተ ክርስቲያናችሁ የደቀመዝሙርነት እና የአመራር እድገት ምን ግንኙነት አላቸው?

14. አንድ ሰው ሌላውን ደቀመዝሙር እንዲያደርገው ብቁ የሚያደርገው ምንድን ነው? አነድን ሰው ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደቱ ማብቂያ ላይ መድረሱ በምን ልታውቁ ትችላላችሁ?

15. በደቀመዝሙርነት ሂደት ውስጥ "መንገር" ***እና*** "ማሳየት" እንዴት ትችላላችሁ?

16. ደቀመዝሙሩ ደቀመዝሙር እንዲሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ደቀ መዝሙር ማድረግ እንዲችል እንዴት ታስታጥቀዋለህ?

17. ለኢየሱስ ያለህን ፍቅርና ታማኝነት የሚቀሰቅሰው ምንድን ነው? ይህንስ ሌሎችን ደቀ መዛሙርት በማድረግ ሂደት ውስጥ እንዴት ማካተት ትችላለህ?

18. በህይወታችሁ የኃጢአትን ኃይል ወይም እሥራት የሚያጠናክር/የሚቀንስ ምንድን ነው?

19. ክርስቶስን ለመከተል የትኞቹ ልምምዶች ወይም ትምህርቶች በጣም አጋዥ ሆነዋል?

## የትግበራ ጥሪ:-

1. ባለፈው አመት እርስዎን ለመቅረጽ ጌታ በህይወትህ ስላደረገው ነገር ሁሉ ሪፖርት ያድርጉ። ደግሞም በሚቀጥለው አመት ባንተ ሕይወት ያደርጋል ብለው ተስፋ ስላደረጉት ነገር ሁሉ ሪፖርት ይስጡ።

2. ቤተ ክርስቲያንህ ምዕመናኗን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ የምታደርገውን ሁሉ ሪፖርት አድርግ። በመጨረሻው የውይይት ቡድን ጊዜ በቡድን ውይይታችሁ መሠረት ለቤተክርስቲያንዎ ወይም ለሚያገለግሉበት አካባቢ የደቀመዝሙርነ የማድረግ ዕቅድ ያቅርቡ።

3. ሌላ አማኝ ደቀመዝሙር ማድረግ ጀምር።

## የባጅ መስፈርት:-

ይህ ባጅ ተማሪው ***ወደ ተግባራዊነት*** የሚለውን የትምህርት ክፍል ከ ***ባጅ አካላት*** እና ***ለውይይት ከቀረቡት ርዕሶች*** አንጻር በታማኝነት እና ባለማቋረጥ በተሳካ ሁኔታ ኮርሱን በሙሉ ሲያጠናቅቅ በአሰልጣኙ ይሸለማል።